*ሕዝቡ፡ እየሰገዱ፡* **“ፈጣሪያችንና አምላካችን! ማርከን! ይቅርም አልኸን! ለኢትዮጵያ፡ እግዚአብሔር መንግሥትም፡ የበቃን አደረግኸን!”** *የሚል ትርጉም ያለውንና እንዲህ የሚለውን መልስ፡ በአንክሮ በተዘክሮ ዜማ ይስጡ!*

**እግዚእነ፥ ወአምላክነ!**
**መሓርከነ ፤ ወተሣሃልከነ፤ ወረሰይከነ ድልዋነ፡ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ዘኢትዮጵያ።**

**“ማቴዎስ፥ ማርቆስ፥ ሉቃስና ዮሓንስ፡ ያወጁትን፡ ቅዱሱን የእግዚአብሔርን የምሥራች ቃል፡ እነሆ ላሰማችሁ!”** *የሚል ትርጉም ያለውናእንዲህ የሚለው መልእክት፡ በካህኑ/በካህኒቱ፡ ልዑል ዜማ ይተላለፍ!*

**ወንጌል ቅዱስ፡ ዘዜነዉ፡ ማቴዎስ፥ ወማርቆስ፥ ሉቃስ፥ ወዮሓንስ፡**
**ቃለ ወልደእግዚአብሔር፡፡**

*ሕዝቡ፡ እየሰገዱ፡* **“ፈጣሪያችንና አምላካችን መሲሕ ሆይ! ኹልጊዜም፡ ለአንተ፡ ምስጋና ይገባሃል!”** የሚል ትርጉም ያለውንና እንዲህ የሚለውን ምላሽ፡ በአንክሮ ተዘክሮ ዜማ ይስጡ!

**ስብሓት ለከ መሲሕ፥ እግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ኵሎ ጊዜ!**

**“የማይሞት ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፥ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ! አቤቱ አዳንኸን! የማይሞት! ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፥ በዮርዳኖስ የተጠመቀ! በዕፀ መስቀል ላይ የተሰቀለ! አቤቱ ሰላምህን ሰጠኸን!”** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው የኪዳን ጸሎት፡ ለእያንዳንዱ የወንጌሉ ምንባብ፡ መግቢያ ተደርጎ፡ በአንክሮ ተዘክሮ የንባብ ድምፅ በካህኑ/በካህኒቱ ይሰማ!*

**ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፥ ዘኢይመውት! ዘተወልደ እማርያም፥ እምቅድስት ድንግል! አድኅንከነ እግዚኦ! ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፥ ዘኢይመውት! ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ! ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል፥ አስተሳለምከነ እግዚኦ!**

*በመጀመሪያ፡ የማቴዎስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **“የካህናት አለቆች፡ ኢየሱስን፡ አሥረው ይዘው፥ ሌሊቱን ሙሉ፡ ሲመክሩበት ካደሩ በኋላ፡ ሲነጋ፡ በወንጀለኛ እንጨት መስቀል ላይ ሊሰቅሉት ተስማምሙ!”** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የአንክሮ የተዘክሮ ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ወጸቢሖ፡ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት፡ ይስቅልዎ ለኢየሱስ ዲበ ዕፀ መስቀል ዘእቡስ፡፡**

## የምንባቦችና ምስባኮች ዝርዝር፡

ከቅዱሳት መጻሕፍት የተውጣጣው፡ የሰሙነ ሕማማት፡ የየዕለቱ ምንባቦችና የአዲስ ኪዳኑ ምስባኮች ዝርዝር፡ ከዚህ የሚከተለው ነው፡-

<u>የሰኞ</u>

<u>፩ኛ፡ እሑድ፥ በምሽቱ፡ ፩ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ሶፎ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፩-፲፪::

ምስባክ፡- መዝ. ፳፯፥ ቁ. ፯-፰::

| | |
|---|---|
| እሴብሕ ወእዜምር ለእግዚአብሔር፤ | ለእግዚአብሔር፡ እቀኛለሁ፤ እዘምርለታለሁ፤ |
| ሰምዓከኒ እግዚኦ ቃልየ ዘሰአልኩ ኀቤከ፤ | አቤቱ፡ ወደአንተ የጮኽሁትን ቃሌን ሰማህ! |
| ተሣሃልከኒ ወሰምዓከኒ፡ ለከ ይብለከ ልብየ:: | ልቤ፡ "ማርኸኝ፥አደመጥኸኝም!" ይልሃል:: |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፳-፴፮::

<u>፪ኛ፡ እሑድ፥ በማታው፡ ፫ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ሶፎ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፲፬-፲፰::

ምስባክ፡- መዝ. ፳፰፥ ቁ. ፮-፯፤ ፰-፱::

| | |
|---|---|
| አድኅንከ ሕዝበከ፥ ወባረክከ ርስተከ፤ | ሕዝብህን አዳንህ! ርስትህንም ባረክህ! |
| ረዐይኮሙ ወአልዐልኮሙ እስከለዓለም፤ | ጠበቅሃቸው፥ እስከዘለዓለምም ከፍ አደረግሃቸው፤ |
| ይትባረክ እግዚአብሔር እስመ ሰምዓኒ ቃለ-ስብሓትየ። | እግዚአብሔር ይመስገን የምስጋናዬን ቃል ሰምቶኛልና። |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፲፰-፳፪::

<u>፫ኛ፡ ሰኞ፥ በሌሊቱ፡ ፮ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ኢዩ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፫-፲፮::

ምስባክ፡- መዝ. ፳፱፥ ቁ. ፩-፪::

| | |
|---|---|
| አምጽኡ ለእግዚአብሔር ውሉደ አማልክት፤ | የአምላክ ልጆች! ለእግዚአብሔር አመጡ! |
| አምጽኡ ለእግዚአብሔር ዕጕለ ሓራጊት፤ | ለእግዚአብሔር፡ የእውነት አምልኮን አመጡ! |
| አምጽኡ ለእግዚአብሔር ክብረ ወስብሓተ:: | ክብርና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አመጡ! |

ወንጌል፡- ማር. ምዕ. ፲፥ ቁ. ፴፪-፴፬::

## ፰ኛ፡ ረቡዕ÷ በማለዳው፡ ፩ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘጸአ. ምዕ. ፲፯÷ ቁ. ፩-፯፤
ኢሳ. ምዕ. ፪÷ ቁ. ፩-፲፩፤
ምሳ. ምዕ. ፫÷ ቁ. ፩-፭::
ሆሴ. ምዕ. ፭÷ ቁ. ፲፫-፲፭::

ምስባክ፡- መዝ. ፹፪÷ ቁ. ፭-፮::

| | |
|---|---|
| እስመ ተማከሩ ኅቡረ ወዐረዩ፤ | በአንተ ላይ፡ በኅብረት ተመሣጥረው ተማከሩ፤ |
| ላዕሌከ ተሰካተዩ ወተካየዱ፤ | ቃል ኪዳናቸውንም፡ በመሓላ አጸኑ፤ |
| ተዓይኒሆሙ ለኤዶምያስ ወለእስማኤላውያን:: | የኤዶማውያንና የእስማኤላውያን ከተሞች። |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፲፩÷ ቁ. ፵፮-፶፬::

## ፱ኛ፡ ረቡዕ÷ በጧቱ፡ ፫ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘጸአ. ምዕ. ፲፫÷ ቁ. ፲፮-፳፪፤
ሲራ. ምዕ. ፳፪::

ምስባክ፡- መዝ. ፵÷ ቁ. ፮-፯::

| | |
|---|---|
| ይባእ ወይርአይ ዘከንቶ ይነብብ፤ | እኔን ለማየት ቢገባ፡ ከንቱን ይናገራል፤ |
| ልቡ አስተጋብአ ኃጢኣተ ላዕሌሁ፤ | ልቡ፡ ኃጢኣትን በላዩ ሰበሰበለት፤ |
| ይወጽእ አፍኣ ወይትናገር ወየኀብር ላዕሌየ:: | ወደውጭ ወጥቶም፡ በላዬ ከተነሡት ጋር ያብራል። |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፳፪÷ ቁ. ፩-፮::

## ፲ኛ፡ ረቡዕ÷ በቀትሩ፡ ፮ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘፀአ. ምዕ. ፲፬÷ ቁ. ፲፫-፴፩፤
ሲራ. ምዕ. ፳፫::

ምስባክ፡- መዝ. ፵÷ ቁ. ፭-፮::

| | |
|---|---|
| ጸላእትየሰ እኩየ ይቤሉ ላዕሌየ፤ | ጠላቶቼ፡ በላዬ ክፉን ይናገራሉ፤ |
| ማእዜ ይመውት ወይሠዓር ስሙ፤ | መቼ ይሞታል? ስሙስ መቼ ይሻራል? ይላሉ፤ |
| ይባእ ወይርአይ ዘከንቶ ይነብብ:: | እኔን ለማየት ቢገባ፡ ከንቱን ይናገራል:: |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፯÷ ቁ. ፴፮-፶::

